# ተፈጥሯዊ ዑደት / በማህፀን ውስጥ የሚደረግ የመፀነስ ሂደት

*ምን እንደሚጠበቅ*

UW Medicine
UNIVERSITY OF WASHINGTON MEDICAL CENTER

*ይህ ጽሑፍ በስነ ተዋልዶ ጤና እና ፅንስ ማዕከል (ሲ. አር. ኤች. ኤፍ. - CRHF) ለሚገኙ ታካሚዎች የተዘጋጀ ነው። "ተፈጥሯዊ ዑደት/በማህፀን ውስጥ የማዳቀል ሂደት" የሚባል የፅንስ ሕክምና እንዴት እንደሚሰራ ያብራራል።*

## ይህ ሕክምና ለማን ነው?

ይህ ሕክምና ከተፈጥሯዊ የመራባት ዑደትዎ ጋር ይሰራል። ከዚህ ሕክምና ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

- ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው ጥንዶች
- ላጤ የሆኑ ታካሚዎች
- ወንድ እና ሴት ሆነው ሳሉ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ የማይችሉ ጥንዶች

## የሕክምና ደረጃዎች

- አንዳንድ ታካሚዎች በዑደቱ መሃል ላይ የማኅፀን አካባቢ አልትራሳውንድ ምርመራ ያደርጋሉ። አልትራሳውንዱ የደረሰ የእንቁላል ከረጢት (ፎሊል) መፈጠሩን ያረጋግጣል። የእንቁላል ከረጢቱ እንቁላል ከመፈጠሩ በፊት የሚያድግ እና የሚደርስ በኦቫሪ ውስጥ የሚገኝ የእንቁላል ከረጢት ነው። የደረሰ እንቁላል ከኦቫሪ ለቆ ሲወጣ ኦቩሌሽን ይባላል።
- የማኅፀን አካባቢ አልትራሳውንድ የተደረገላቸው ታካሚዎች እንቁላሉ በደንብ ለፍሬ እንዲበቃ እና መቼ በማህፀን ውስጥ ፅንስ የሚፈጠርበትን ጊዜ የሚወስን እንቁላላሉን የሚያነቃቃ መርፌ (ovulation *trigger injection*) ሊጠቀሙ ይችላሉ።
- አንዳንድ ታካሚዎች የቤት ውስጥ የእንቁላል ቅድመ-ምርመራ ኪት (ኦ.ፒ.ኬ. - OPK) እስከ ጽንስ መፈጠሪያ ጊዜ ድረስ ይጠቀማሉ። ኦ.ፒ.ኬ. ሲጠቀሙ የአልትራሳውንድ ወይም እንቁላሉን የሚያነቃቃ መርፌ አያስፈልግዎትም። በየቀኑ በተመሳሳይ ጊዜ ኦ.ፒ.ኬ. ያደርጋሉ። አብዛኛዎቹ ታካሚዎች በወር አበባ ዑደታቸው በ10ኛው ቀን ኦ.ፒ.ኬ.ዎችን መመርመር ይጀምራሉ።
  - እኩለ ቀን በፊት ሽንት ሲሸኑ ለሁለተኛ ጊዜ ምርመራ እንዲያደርጉ እንመክራለን።
  - የመጀመሪያውን የኦ.ፒ.ኬ. ውጤትዎ ፖዘቲቭ ሲሆን፣ በሚቀጥለው ቀን ፅንስ ለማዳቀል ከሰዓት በፊት ወደ ሲ.አር.ኤች.ኤፍ. መደወል አለብዎት።



***ያየእንቁላል ከአቫሪ መውጣትን መተንበ ኪቶች ለማዳቀል ትክክለኛውን ጊዜ ለመወሰን ይረዳሉ።***

## የ አይ.ዩ.አይ. (IUI) ሂደት

በራሱ በጣም ተንቀሳቃሽ የሆነ የወንድ የዘር ፍሬ እንቁላሉን (እንቁላሎቹን) በጣም ስለሚቀርበው/ባቸው **በማህፀን ውስጥ የሚፈጸምን የፅንስ መፈጠር** እድል እውን ያረጋዋል። ይህም የእርግዝና እድልን ይጨምራል።

የ አይ.ዩ.አይ. አሰራር በአንጻራዊነት ቀላል ነው። የወንድ የዘር ፍሬ (ስፐርም) ናሙና ዝግጁ ከሆነ በኋላ ጥቂት ደቂቃዎችን ብቻ ይወስዳል። የወንድ የዘር ፍሬው ይታጠባል፣ ይህም ጤናማውን የወንድ የዘር ፍሬ ከሌሎች ፈሳሾች ይለያል። ይህም የእርግዝና እድልን ለመጨመር ይረዳል።

- በምርመራ ጠረጴዛ ላይ ይተኛሉ።
- የሕክምና ባለሙያዎ የማህፀን ጫፍዎን ማየት እንዲችሉ በሴት ብልትዎ ውስጥ ስፔኩለምን በቀስታ ያስገባል።
- ቀጭን፣ የሚተጣጠፍ ካቴተር (ቱቦ) በማህጸን ጫፍዎ በኩል ወደ ማህፀንዎ ያስገባሉ። የታጠበው የወንድ የዘር ፈሳሽ ናሙና ቀስ ብሎ ይወጋል።
- ብዙውን ጊዜ ይህ አሰራር ህመም የለውም፣ ነገር ግን አንዳንድ ታካሚዎች መለስተኛ ቁርጠት አለባቸው። ከ አይ.ዩ.አይ. በኋላ ለ1-2 ቀናት መንጠባጠብ (ቀላል የደም መፍሰስ) ሊያጋጥሙዎት ይችላሉ።

## ሊሆኑ የሚችሉ አደጋዎች ምንድናቸው?

የ አይ.ዩ.አይ. አደጋዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:-

- **የመፀነስ አደጋዎች:-** የመኮማተር፣ የመንጠባጠብ ወይም የኢንፌክሽን አደጋ (በጣም አልፎ አልፎ)፤
- **የውደት መሰረዝ:-** የእንቁላል ከረጢቶቹ በአግባቡ ካላደጉ ወይም እንቁላል ከአቫሪ መውጣት ያለጊዜው ከተከሰተ የሕክምና ዑደቱ ይሰረዛል።

### ጥያቄዎች?

ጥያቄዎችዎ አስፈላጊ ናቸው። ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉዎት ሐኪምዎ ወይም የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይደውሉ።

**የስነ ተዋልዶ ጤና እና የጽንስ ማዕከል:**

**በስራ ቀናት ከጠዋቱ 8 ሰዓት እስከ ምሽቱ 5 ሰዓት:** በ206.598.4225 ይደውሉ

**ከስራ ሰዓት በኋላ፣ ቅዳሜና እሁድ እና በዓላት:** በ206.598.6190 ይደውሉ እና በጥሪ ላይ ያለውን የሲ.አር.ኤች.ኤፍ. በስራ ቀናት ከጠዋቱ 8 ሰዓት እስከ ምሽቱ 5 ሰዓት: በ206.598.4225 ይደውሉ።

© University of Washington Medical Center
Published PFES: 2015, 2016, 2025
Clinician Review: 05/2025
Reprints on Health Online: https://healthonline.washington.edu

# Natural Cycle / Intrauterine Insemination

*What to expect*

*This handout is for patients at the Center for Reproductive Health and Fertility (CRHF). It explains how a fertility treatment called "natural cycle/intrauterine insemination" works.*

## Who is this treatment for?

This treatment works with your natural fertility cycle. People who might benefit from this treatment include:

- Same-sex couples
- Single patients
- Heterosexual couples that are not able to have sexual intercourse

## Treatment Steps

- Some patients have a **pelvic ultrasound** exam in the middle part of the cycle. The ultrasound confirms that a mature *follicle* has formed. The follicle is an egg sac within the ovary that grows and matures before *ovulation* occurs. Ovulation is the release of a mature egg from the ovary.
- Patients who have a pelvic ultrasound may also use an ovulation *trigger injection* (shot) which helps the egg mature and determines the time your intrauterine insemination should occur.
- Some patients use a home ovulation predictor kit (OPK) to time insemination. When using an OPK, you will not need an ultrasound or ovulation trigger injection. You will check an OPK at the same time each day. Most patients begin checking OPKs on the 10th day of their menstrual cycle.
  - We recommend that you test the 2nd time you urinate (pee) before noon.
  - When you get your first positive OPK result, you must call CRHF before noon in order to have an insemination the next day.



***Ovulation predictor kits can help you determine the right time for insemination.***

## The IUI Procedure

**Intrauterine insemination** (IUI) places the most *motile* (moving) sperm as close as possible to the egg(s) when fertilization is most likely. This helps increase the chance of pregnancy.

*Scan for a digital copy of this handout.*


Center for Reproductive Health and Fertility | Box 354780
4245 Roosevelt Way N.E., 3rd floor, Seattle, WA 98105 | 206.598.4225

The IUI procedure is relatively simple. It only takes a few minutes once the semen (sperm) sample is ready. The semen sample will be *washed*, which separates the healthy sperm from other fluids. This helps increase the chance of pregnancy.

- You will lie on an examining table
- Your provider will gently insert a speculum into your vagina so they can see your cervix.
- They will insert a thin, flexible catheter (tube) through your cervix and into your uterus. The washed semen sample is slowly injected.
- Usually this procedure is painless, but some patients have mild cramps. You may experience spotting (light bleeding) for 1-2 days after the IUI.

## What are the possible risks?

The risks of IUI include:

- **Insemination risks:** Cramping, spotting, or infection (very rarely).
- **Cycle cancellation:** If the follicles don't grow properly or ovulation happens too early, the treatment cycle will be cancelled.

## Questions?

Your questions are important. Call your doctor or healthcare provider if you have questions or concerns.

**Center for Reproductive Health and Fertility:**

**Weekdays 8 am – 5 pm:** Call 206.598.4225

**After hours, weekends, and holidays:** Call 206.598.6190 and ask to page the CRHF provider on call.

© University of Washington Medical Center
Published PFES: 2015, 2016, 2025
Clinician Review: 05/2025
Reprints on Health Online: https://healthonline.washington.edu